ጥር 10/2003 ዓ.ም

# መኢአድ መሠረታዊ የሆነ አስቸኳይ መፍትሔ ይሻል!

## (ከመኢአድ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ የተሠጠ መግለጫ)

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በርካታ ኢትዮጵያውያን ውድና ክቡር ህይወታቸውን የከፈሉበት፣ የታሰሩበት፣ የተገረፉበት፣ አካላቸው የጎደለበት፣ ቤት ንብረታቸውን ያጡበት፣ ከሥራ ገበታቸው የተፈናቀሉበትና ከሃገር የተሰደዱበት ፓርቲ ነው፡፡ መኢአድ በነፃነት ፈላጊ ኢትዮጵያውያን ደም የተመሠረተ ህብረ ብሔራዊ ድርጅት ነው፡፡

በታላቅ መስዋዕትነት የተመሠረተውን ፓርቲያችንን እንደ ዓይናችን ብሌን ልንንከባከበውና ልንጠብቀው ያስፈልጋል፡፡ እንዲህ ስናደርግ ነው የተነሳንለትን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን በኢትዮጵያ የማስፈን ብሩህ ዓላማ ከግብ የምናደርሰው፡፡

መኢአድ በአሁኑ ወቅት ውስብስብ በሆኑ በርካታ ችግሮች ውስጥ ይገኛል፡፡ የፓርቲያችን ህልውና ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ የችግሩ ፈጣሪዎች በከፍተኛ አመራር ላይ ያሉና ቅንነት የሌላቸው፣ ታማኝ ያልሆኑ፣ ለግል ጥቅማቸው ያደሩና የሥልጣን ጥም ያናወዛቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡ እነዚህ አመራሮች አባላትን ያለ አግባብ የማገድና የማባረር፣ በፓርቲው ውስጥ ጠንካራ ሰዎች እንዳይሠሩ እንቅፋት የመፍጠር፣ የፓርቲው ሥራ በአግባቡ እንዳይከናወን የማድረግ፣ በፓርቲው ገንዘብ አለአግባብ የመጠቀም፣ በጥቅም በመተሳሰር ቡድን የመፍጠር፣ በጎጥ በመሰባሰብ መንደርተኝነትን የማስፋፋት እና የመሳሰሉት እኩይ ተግባራት በማከናወን ፓርቲውን እየጎዱት ይገኛሉ፡፡

የግለሰቦቹን ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶች በመቃወም ቀደም ካሉ ዓመታት ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ ለመኢአድ ፕሬዚዳንት ለኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በደብዳቤ አሳውቀናል፤ በቃልም ቅሬታችንን አሰምተናል፡፡ መፍትሔ እንዲደረግባቸው ካቀረብናቸው ሃሳቦች ለአብነት ያህል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ነበሩ፡፡ እነዚህም÷

1. ፓርቲው በጠቅላላ ጉባዔ ወይም በላዕላይ ም/ቤት አባላት የፀደቀ ህገ ደንብና ፕሮግራም ይኑረው፤
2. የድርጅቱ የገንዘብ አጠቃቀም ሥርዓት የፋይናንስ ህግን የተከተለ ሆኖ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው ይሁን፡፡ ሂሳቡ በውጭ ኦዲተር ይመርመር፤
3. ለፓርቲው ሥራ በተገቢው ቦታ ተገቢ ሰው ይቀመጥ፤
4. የፓርቲው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቁጥሩ ያልተሟላ በመሆኑ የላዕላይ ምክር ቤቱ ተሰብስቦ በህግ አግባብ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ይሟላ፤

5. በህገ ወጥ መንገድ በተለያዩ ሁኔታዎች ከፓርቲው እንዲወጡ የተደረጉ ጠንካራ አባላት በሙሉ ጥሪ ተደርጎላቸው ችግሮች በውይይት ይፈቱ የሚሉና ሌሎችም ነበሩ።

በፓርቲው ውስጥ ለችግሮቹ መፍትሔ ከመሻት ይልቅ ችግሮቹ እንዲወገዱ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሁሉ የሚያሳስቡትን ሃቀኛና እውነተኛ የድርጅቱ ታጋዮችን በህገ ወጥ መንገድ ከፓርቲው እንዲለቁ ተደረገ። ለችግሮቹ ምንም መፍትሔ ሳይፈለግላቸው ቀርቶ ፓርቲያችን ዛሬ እዚህ አሁን የደረሰበት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶ ለማየት በቃን።

የመኢአድ አመራር የፓርቲውን ችግሮች በመሸፋፈንና ለችግሮቹ መፍቻ ምንም መላ ሳያበጅ በህገ ወጥ መንገድ ጠቅላላ ጉባዔ ጠርቶ ከዚህ በፊት በፓርቲው ላይ እንቅፋት ሲፈጥሩ የነበሩት ግለሰቦች አሁንም በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት እንዲቀጥሉ አደረገ። የመኢአድ አመራሮች በሁለት ጎራ ተከፋፍለው ተገቢ ያልሆኑ ቃላት በመወራወር ያካሄዱት ሁካታ የጉባዔውን ጸጥታ ሲያደፈርስ ቆይቷል። ሴራ የተሞላው ተግባራቸው በጠቅላላው ጉባዔው ስብሰባ ላይ እንኳን ሳይቀር ጎልቶ ወጥቶ ጉባዔውን አሳዝኗል።

በፓርቲያችን ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃ ላይ የነበርን አባላት ፓርቲው አደጋ ውስጥ መኖሩን በመገንዘብ በመኢአድ ውስጥ ያሉት ችግሮች መፍትሔ ማግኘት አለባቸው ብለን **የመኢአድ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አቋቁመናል። በዚህም ፓርቲያችንን ከተጋረጡበት የመሰነጣጠቅ አደጋ ለመታደግ የምንችለውን ሁሉ በማድረግ ላይ እንገኛለን።**

የመኢአድ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ ፓርቲውን ወደአዘቅት እያወረዱ ያሉት ግለሰቦች በድጋሚ በአመራርነት እንዲቀጥሉ መደረጋቸውን ተቃውሞ እና በተለያዩ ምክንያቶች ከፓርቲው የተገለሉ አባላት በመኢአድ ጉዳይ ላይ አብረው እንዲመክሩ ጥሪ እንዲደረግላቸው አሳስቦ መግለጫ አውጥቷል።

መግለጫውንም የመኢአድ ጠቅላላ ጉባዔ በተካሄደበት ሥፍራ ተገኝቶ ለጋዜጠኞች አሰራጭቷል። ለፓርቲው ፕሬዚዳንትም ልኳል።

የመኢአድ ጠቅላላ ጉባዔው በተካሄደ ማግስት አመራሩ ቀድሞ የነበረውን የሁለት ቡድኖች (የአቶ ያዕቆብ ልኬና የአቶ ማሙሸት አማረ) ጎራ አጠናክሮ የእርስ በርስ መጠላለፉንና መላተሙን ቀጠለ። ይኸውም የፓርቲውን ሥም በሚያጎድፍና ደረጃውን ዝቅ በሚያደርግ ሁኔታ አንዱ ቡድን በሌላው ላይ ቢሮ መቆለፍ፣ እርስ በርስ መሰዳደብና መዘላለፍ፣ መደባደብና ሌሎችንም አሳፋሪ ድርጊቶች ፈጸሙ። ሁለቱም ቡድኖች በየፊናቸው የሌላውን ቡድን አባላት አገድን አሉ። ለየራሳቸውም የኃላፊነት ድልድል አደረጉ። የንብረት ዘረፋም ተካሄደ። ግጭቱ አልበርድ በማለቱም ፖሊስ ጉዳዩን እየተከታተለው ይገኛል።

በፓርቲው አመራር መካከል እየተፈጸመ ያለው ችግር ተባብሶ ከዚህም በላይ ከመድረሱ **በፊት የመኢአድ ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል መፍትሔ ለመሻት ዕድሉ ስላላቸው**

የሚከተሉትን ጉዳዮች እንዲፈጽሙ እንጠይቃለን። ለጥያቄዎቻችንም በጎ ምላሽ እንዲሰጡን በኢትዮጵያ ህዝብና በሃገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማስፈን ሲሉ መስዋዕትነት በከፈሉ ወገኖቻችን ሥም እንማጸናለን።

እነዚህም፦

<u>1.ጉዳዮችን የሚያጣራና የመፍትሔ ሃሳብ የሚያቀርብ ኮሚቴ ማቋቋም፣</u>

በቡድን ተከፋፍለው የፓርቲውን ክብርና ዝና በሚቀንስና በሚያጎድፍ መንገድ የሚደረጉት እንቅስቃሴዎች በአስቸኳይ ይቆሙ ዘንድ ችግሩን የሚያጣራና የመፍትሔ ሃሳብ የሚያቀርብ አቢይ ኮሚቴ ማቋቋም፣ (በዚህ ላይ ገለልተኛ የሆኑ አባላት የመፍትሔው አካል እንዲሆኑ ማሳተፍ ወሳኝነት አለው።)

<u>2. የፓርቲው ሰነዶችና ንብረቶች እንዲጠበቁ ማድረግ፣</u>

በመኢአድ ጽ/ቤት ውስጥ የሚገኙት ሰነዶችና ንብረቶች ለፓርቲው ጠቃሚዎችና መስዋዕትነትም የተከፈለባቸው መሆናቸው ይታወቃል። በአሁን ወቅት በአመራሩ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ጉዳት እንዳይደርስባቸው ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው፣

<u>3. ከፓርቲው ከተገለሉ ሰዎች ጋር ውይይት ማድረግ፣</u>

አመራሩ በፈጠራቸው ሳንካዎች ምክንያት ከፓርቲው የራቁ እንዲሁም በህገ ወጥ መንገድ ከድርጅቱ እንዲገለሉ ከተደረጉ ከፓርቲው አባላት ጋር (የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትን ጨምሮ) ያለው ጠቅላላ ችግር እንዲፈታ ውውይት ማድረግ፣

<u>4. ጠቅላላ ጉባዔ ባስቸኳይ መጥራትና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ፣</u>

ለችግሩ ዋና መንስዔ የሆነው በህገ ወጥ መንገድ የተካሄደው ጠቅላላ ጉባዔና የአመራር ምደባ በመሆኑ በትክክለኛ መንገድ ጠቅላላ ጉባዔ በአስቸኳይ እንደገና መጥራት እና ዲሞክራሲያዊ የሆነ እውነተኛ ምርጫ ማካሄድ፣

<u>5. በአባላት መካከል ዕርቅ እንዲፈጠር መድረክ መፍጠር፣</u>

በሃር ቤትም ሆነ በውጭ ሃገር በሚገኙት አባላትና ደጋፊዎች መከፋፈል የተፈጠሩ ልዩነቶችን አስመልክቶ ሊያስማማ የሚችል ሁሉንም ያካተተ ውይይትና ዕርቅ ማድረግ የሚያስችል መድረክ እንዲፈጠር ማድረግ፣

ከላይ የተገለጹትንና ሌሎችንም መሰል የመፍትሔ ሃሳቦችን የመኢአድ ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በማስተዋልና አርቆ በማሰብ ተግባራዊ እንዲያደርጓቸው አጥብቀን እንጠይቃለን።

**በሃገር ውስጥ በገጠርና በከተማ የምትገኙ አባላት!**

**እንዲሁም በውጭ ሃገር የምትኖሩ የመኢአድ ደጋፊዎችና አባላት!** መኢአድ በአሁን ወቅት ለገጠመው ችግር መፍትሔ በመፈለግ የድርሻችሁን እንድትወጡ እናሳስባለን። የአደራ ጥሪም እናቀርባለን።

**ውድ ወገኖቻችን!**

**በመጨረሻም የመኢአድ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ ፓርቲያችን ችግሮቹ ሁሉ ተወግደው ወደ ነበረ ክብሩ እስኪመለስ ድረስ መፍትሔ የመሻቱን ሥራ እስከመጨረሻ ይገፋበታል፡፡ ስለዚህ <u>የመኢአድ ጉዳይ ጉዳያችን ነው የምትሉ</u> በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከጎናችን ቆማችሁ የመፍትሔው አካል እንድትሆኑ የአክብሮት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡**

*መኢአድን ከውድቀት ለማዳን በጋራና በቅን ልቦና እንሥራ!!!*

*እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!!!*

*<u>የመኢአድ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ</u>*